Health
South Eastern Sydney
Local Health Network



# ሺስቶሶማያሲስ

SCHISTOSOMIASIS

## ሺስቶሶማያሲስ ምንድ ነው? (What is Schistosomiasis?)

- ሺስቶሶማያሲስ ቢሊሃርዝያ (Bilharzia) በመባልም ይታወቃል፣ ይህ በሽታ የሚመጣው ጨው አልባ በሆነ ውሃ ውስጥ በሚገኙ ጥቃቅን ትሎች ነው።
- በበሽታው ሊያዙ የሚችሉት ታዳጊ ትሎቹ ከቆዳዎት ጋር ሲገናኙ ነው።
- ትሎቹ ቆዳን ሰርስረው በመግባት ወደ ሳንባና ጉበት ይጓዛሉ፣ እዚያ ውስጥም ከአደጉ በኋላ እንቁላላቸውን መፈልፈል ይጀምራሉ።
- ትሎቹ በደም ቧንቧ፣ በፊኛ ወይም በአንጀት ውስጥ ለብዙ ዓመታት መኖር ይችላሉ።
- ሕክምና ካልተደረገ ትሎቹና እንቁላላቸው በጉበት፣ በአንጀትና በፊኛ ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ። አልፎ አልፎም እንደ እንፍርፍሪት (የሚጥል በሽታ) ዓይነት ችግሮችን ያስከትላሉ።

## የሚያስከትለው አደጋ ምንድን ነው? (Who is at risk?)

- ጨው አልባ በሆነ ውሃ፣ የሺስቶሶማያሲስ ትሎች በሚገኙበት አገር (ለምሳሌ፣ በአንዳንድ የአፍሪካ አገሮች፣ በካሪብያን፣ በደቡብ ቻይና፣ በደቡብ-ምስራቅ እስያና በመካከለኛው ምስራቅ) ውስጥ ኖረው ወይም ተጉዘው የሚያውቁ ከሆነ በበሽታው ተይዘው ሊሆን ይችላል።
- ሰዎች ጨው አልባ በሆነ የውሃ መስኖዎች፣ ጅረቶችና ሃይቆች ውስጥ የተለያዩ ሥራዎችን ሲያከናውኑ ለምሳሌ፣ ውሃ ሲቀዱ፣ ግብርና ሲሰሩ ወይም አሳ ሲያጠምዱ በበሽታው በቀላሉ ሊያዙ ይችላሉ።

## የህመሙ ምልክቶች ምንድን ናቸው? (What are the symptoms?)

- አንዳንድ ሰዎች ከተያዙ ከጥቂት ቀናት በኋላ በቆዳቸው ላይ ሽፍታ ይወጣል ወይም ያሳክካቸዋል።
- በሚቀጥሉት ተከታታይ ሳምንታት ውስጥ ትኩሳት፣ የራስ ምታት፣ ሣሳልና የጡንቻ ሕመም ይሰማቸዋል።
- ምንም እንኳን ትሎቹ በውስጣቸው እያሉና እንቁላል እየጣሉ ብዙ ሰዎች የበሽታውን ምልክቶች በፍጹም አያሳዩም።

## እንዴት ነው ተመርመሮ ሊታወቅ የሚችለው? (How is it diagnosed?)

- በሺስቶሶማያሲስ ተይዘው ያውቁ እንደሆነ በደም ምርመራ ይታወቃል።
- በሽታው እንዳለብዎት በምርመራው ከተረጋገጠ፣ እንቁላሎቹን ለማየት እንዲቻል ለሽንትና ሰገራ ምርመራ ናሙና እንዲሰጡ ይጠየቃሉ።
- እንቁላሎቹ ከተገኙ ተጨማሪ ምርመራ (ለምሳሌ፣ ኤክስሬ) ማድረግ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

## ለበሽታው ሕክምና የሚሰጠው እንዴት ነው? (How is the infection treated?)

- ሺስቶሶማያሲስን በሚገባ ለማከም ተስማሚና አጥጋቢ ውጤት የሚሰጡ መድኃኒቶች አሉ።
- በደም ምርመራ በሽታው ለተገኘባቸው ብዙ ሰዎች ኪኒን ይሰጣቸዋል።
- በሽንትዎ ወይም በሰገራ ውስጥ እንቁላሎች ከተገኙ ሁለተኛ ዙር ሕክምና አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

ተጨማሪ ማብራሪያ ከሚከተለው ማግኘት ይችላሉ፤ (Further information is available from)